# የህሊና ጉንተላዎች

አብርሃም በየነ

ቤዝ አሲምባ ፀለምት - ዶሎኪያ ተርናሻ፣

መሰረት ያኖርኩት - መነሻ መድረሻ፣

አንዱን ላውሬ ጥሎ - ሌላዋን ለውሻ፣

ስደት አድርጎታል - ህይዎቴን መሸሻ።

* * * *

እናንት ወንድሞቼ፣

እናንት እህቶቼ፣

ጠላት አሰፍስፎ - ሰውርና ይፋ፣

ንቁ አናንቀላፋ፣

እኛም ዝምታውን - አበዛነው መሰል፣

ሁሉም ያነደናል እንደ ድንጊያ ከሰል።

* * * *

እንካ ባለክራር......

ግጥም ተቀበለኝ፣

ፍትህ የተጠማሁ - ነፃነት የራበኝ፣

ዕዝልና አራራይ - አድርገህ አዚመው፣

ወደ ላይ ወደ ታች - አንሳውና ጣለው፣

ቃኘው ባለክራር......

ቼ- በለው ቼ - በለው፣

ልቤን ማርከውና - በሙዚቃ አስክረው፣

በክራርህ ቅኝት - በጣቶችህ ጫፍ ላይ፣

ስመኝ እኖራለሁ - በህይዎቴ ድል ላይ።

* * * *

በክፉው ዘመን ወቅት - በዚያ በዘግናኙ፣

በነፃነት ትግል - ገብተው እየዋኙ፣

ለተበደሉና አቅመ ቢስ ለሆኑት፣

ጠበቃ እየቆሙ - ህይዎት ለከፈሉት፣

ነግ ከነገ ወዲያም - እሰከ ዘለዓለሙ፣

ማስታዎሻ ይሁን - የደም ቀይ ቀለሙ።

* * * *

የሚተካን ትውልድ - ዐይኑ የታወረ፣

በዘር ሃረግ መንገድ - ጥምል እየዞረ፣

የመንደርተኛ ቡን - በጎጥ እየጠጣ፣

ጫት ያመነዥካል - ቅጠል እንደ ጠጣ።

* * * *

ተማምለን ነበር - ፍፁም ነው ዕምነቴ፣

ቃልኪዳን ነበረን - ትግሉ ነው ሕይዎቴ፣

ማተቡን ፈትቶ - ከሃዲ ከዳና፣

አስገብቶን ጠፋ - በደም ባህር ዋና።

* * * *

ኢሕአፓ ሲገደል....

ለምን ሞተ ቢሉ፣

ታሪኩን በነቂስ ንገሩ ለሁሉ፣

ያብዮት ዘመቻ ሞት - ያረገው ስንቁን፣

የሕዝብ ድርጅት...... ቀይ ሽብር ይልቁን፣

እርሱን ብቻ ነበር - ከዜጎቹ አብልጦ፣

ቋጥሮ የተሸኘው - ኢትዮጵያዊ መርጦ።

* * * *

አንቺ የፀደይ አበባ....

የንቦች ቀሰም አጥቢያሽ፣

ፍንድቁ ሲፈካ ቦራሽ፣

የፀደይ ጥባቱ ፀዳል፣

ጨፈጉ ፈተት - ቢ- ሲል፣

ለኛ ነጋ መስከረም ጠባ፣

አዶዮው ፈካ ፈነጠቀ፣

ያንቺው ጀንበር ግን ጠለቀ።

* * * *

ሞተዋል ይሉናል - ከሞትን ባገሩ፣

ህዝቡ ከቀበረን - ከተሜው ገጠሩ፣

ኢሕአፓ ሲነሳ - የ 'ሞተ' አካል ፈርተው፣

ቀን ሲደነግጡ - ሌሊት እንቅልፍ አተው፣

ለምን ይኖራሉ - ዘወትር ባትተው ?

* * * *

ሸበቶውን ዘመን - ግንደ ቆርቁር ሆኜ፣

በዘመናት ትግል - በውስጡ ሸፍቼ፣

ፋሽሽቱን አገዛዝ - ቋያ እሳት ለኩሼ፣

በሰደድ-ነበልባል - አመፅ ተሟግቼ፣

የዘሩን ዘመን ግን - እግሬ ነቅሎ ሂዶ፣

ሳርር እገፋዋለሁ - ውስጥ አንጀቴ ነዶ !!

ግንቦት 2002